moj
Ministry of justice

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፫
አዲስ አበባ–ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 53
ADDIS ABABA - 30th June, 1998

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፻፳፫/፲፱፻፺ ዓ·ም·
የመከላከያ ሠራዊት (ማሻሻያ) አዋጅ ........... ገጽ ፯፻፹፱

CONTENTS

Proclamation No. 123/1998
Defence Forces (Amendment)
Proclamation ...................................... Page 789

### አዋጅ ቁጥር ፻፳፫/፲፱፻፺
### የመከላከያ ሠራዊት አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የመከላከያ ሠራዊት አዋጅን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፯) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የመከላከያ ሠራዊት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፻፳፫/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር ፳፯/፲፱፻፹፰ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

፩· የአንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሠርዞ ፣ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ሆነዋል ።

፪· የአንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል ፣

"፫· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከቱት የሥራ መሰናበቻ ዕድሜ ጣራዎች ለጡረታ ሕግ አፈጻጸም የጡረታ መገለያ ዕድሜ ሆነው ይቆጠራሉ።"

፫· አንቀጽ ፲፭ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፭ ተተክቷል፣

### PROCLAMATION NO. 123/1998
### A PROCLAMATION TO AMEND THE DEFENCE FORCES PROCLAMATION

WHEREAS, it is found necessary to amend the Defence Forces Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (7) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Defence Forces (Amendment) Proclamation No. 123/1998."

2. *Amendment*

The Defence Forces Proclamation No. 27/1996 is hereby amended as follows:

1) Sub-Article (2) of Article 9 is deleted while sub-Articles (3) and (4) are renumbered as sub-Articles (2) and (3), respectively.

2) Sub-Article (3) of Article 13 is deleted and replaced by the following new sub-Article (3):

"3) The age-limits for termination of service, specified under sub-Articles (1) and (2) of Article 9 hereinabove, shall also be deemed to be retirement age-limits for purposes of the application of pension laws."

3) Article 15 is deleted and replaced by the following new Article 15:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

moj Ministry of justice



"፲፭· ሜዳይ ፥ ኒሻንና ሽልማት

ማንኛውም የሠራዊቱ አባል በዚህ አዋጅ ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጐችና መመሪያዎች መሠረት ለፈጸመው አገልግሎትና ጀግንነት እንዲሁም ለአዲስ ግኝት ወይም የፈጠራ ሥራ ሜዳይ፥ ኒሻን ወይም ሽልማት እንዲያገኝ ይደረጋል ።"

፬· አንቀጽ ፳፩ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፩ ተተክቷል ፤

"፳፩· የግዴታ አገልግሎት

አንድ የሠራዊት አባል ልዩ ሥልጠና ወይም ትምህርት እንዲያገኝ ከተደረገ ሥልጠናውን ወይም ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ ሥልጠናው ወይም ትምህርቱ የወሰደውን ጊዜ እጥፍ የማገልገል ግዴታ አለበት ፤ ሆኖም የዚህ ዓይነቱ የግዴታ አገልግሎት ከአንድ ዓመት ሊያንስ አይችልም ።"

፭· አንቀጽ ፴፫ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፫ ተተክቷል ፤

"፴፫· ስለምርመራና ክስ አመሠራረት

፩· አንድ ጉዳይ ወታደራዊ ፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት ጥልቅና ገለልተኛ የሆነ ምርመራ መካሄድ አለበት ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አንድ ጉዳይ ለምርመራ እንዳስፈላጊነቱ ለአንድ መርማሪ፥ በቡድን እንዲሠሩ ለተመደቡ መርማሪዎች ወይም ለፖሊስ ሊመራ ይችላል ።

፫· የምርመራ ውጤቱ ክስ ለመመሥረት የሚያስችል ሆኖ ሲገኝ ጉዳዩ አግባብ ላለው ወታደራዊ ፍ/ቤት ይመራል ፤ ክሱን የሚከታተል ዐቃቤ ሕግም ይመደባል ።"

፮· ከአንቀጽ ፴፮ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ክፍል ስድስት ተጨምሯል፡

"ክፍል ስድስት

ሜዳይ ፥ ሪባንና የምስክር ወረቀት የሚያስገኙ ሁኔታዎችና የተሸላሚዎች ልዩ መብቶች

፴፯· ሜዳዮች ፥ ሪባንና የምስክር ወረቀት

፩· ለመከላከያ ሠራዊት አባላት የሚሰጡ ሜዳዮች ፥ ሪባንና የምስክር ወረቀት የሚከተሉት ናቸው ፤

ሀ) የአድዋ ድል ሜዳይ ፤
ለ) የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ፤
ሐ) የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ ፤
መ) የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ፤
ሠ) የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ባለዘንባባ ፤
ረ) የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ያለዘንባባ ፤
ሰ) የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ ፤
ሸ) የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ፤
ቀ) የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ ፤
በ) የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ፤
ተ) ዓለምአቀፍ የሠላም ማስጠበቅ ሜዳይ ፤
ቸ) የአውደ ውጊያ ቁስለኛ ሜዳይ ፤
ኀ) የውትድርና አገልግሎት ሪባን ፤
ነ) የውጊያ ተሳትፎ የምስክር ወረቀት።

"15. *Medals, Orders and Prizes*

Any member of the Defence Forces shall be awarded with Medals, Orders or Prizes for notable service, heroism as well as for new findings or creative work in accordance with this Proclamation or other relevant laws and directives."

4) Article 21 is deleted and replaced by the following new Article 21:

"*21 Obligatory Service*

A member of the armed forces having received the benefit of specialized training or schooling shall, subsequent to its completion, have the obligation to serve twice of the duration of schooling or training; however, such an obligatory services cannot be less than one year."

5) Article 33 is deleted and replaced by the following new Article:

"*33. Investigation and Suit*

1) Intensive and impartial investigation shall be carried out prior to bringing a case before a military court.
2) A case for investigation, pursuant to sub-Article (1) of this Article, may be referred to a soldier or a team of soldiers or to the police as necessary.
3) Where it is necessary to bring a charge the case shall be referred to the appropriate military court. A public prosecutor will be assigned to follow up the case."

6) A new Part Six is added after Article 36.

"*Part six*

*Medals, Ribbons, and Certificates Privileges due to Awardees*

*37. Medals, Ribbons and Certificates*

1) The following are Medals, Ribbons and Certificates to be bestowed upon Members of the Defence Forces:
   (a) The Medal of the Victory of Adwa;
   (b) The Medal of Heroism 1st Rank;
   (c) The Medal of Heroism 2nd Rank;
   (d) The Medal of Heroism 3rd Rank;
   (e) The Medal with Palm Leaf for Participation in the Armed Struggle;
   (f) The Medal without Palm Leaf for Participation in the Armed Struggle;
   (g) The Medal of Distinguished Labour;
   (h) The Medal of Military Service 1st Rank;
   (i) The Medal of Military Service 2nd Rank;
   (j) The Medal of Military Service 3rd Rank;
   (k) The Medal of International Peace Keeping;
   (l) The Medal of the Wounded;
   (m) The Military Service Ribbon;
   (n) Combat Certificate.

moj Ministry of justice



፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሜዳዮች፣ ሪባንና የምስክር ወረቀት መጠን ፡ ቅርጽና ይዘት በሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ ይወሰናል ።

፴፰· የአድዋ ድል ሜዳይ

፩· የአድዋ ድል ሜዳይ ወደር የሌለው ጀግንነት በአውደ ውጊያ ለፈጸመ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም የሠራዊት አሀድ ወይም ቡድን የሚሰጥ የመጨረሻ ከፍተኛ የጀግና ሽልማት ነው ።

፪· የአድዋ ድል ሜዳይ የተሸለመ ሰው ፤

ሀ) በሕይወት ያለ ከሆነ ብር ፳፭ሺ የአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጠዋል ፤ ከሞተም በጡረታ ሕግ በተመለከተው መጠን መሠረት ለወራሾቹ ብር ፳፭ሺ ይከፈላል ፤

ለ) በብሔራዊ በዓል አከባበር ሥነ–ሥርዓት ወቅት ለከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል ፤

ሐ) በርዕሰ ብሔሩ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል ፤

መ) በትውልድ ሥፍራው ትምህርት ቤት ፤ ሆስፒታል ፤ መንገድ ፤ አደባባይ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መጠሪያ ሊሰየምለት ይችላል ።

፫· የአድዋ ድል ሜዳይ ሁለት ጊዜ የተሸለመ ሰው በፌዴራሉ ዋና ከተማ ትምህርት ቤት ፤ ሆስፒታል፣ መንገድ ፤ ድልድይ ፤ አደባባይ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መጠሪያ በስሙ ሊሰየምለት ይችላል ፤ በተጨማሪም መታሰቢያ ሐውልት ሊቆምለት ይችላል ።

፬· የአድዋ ድል ሜዳይ ተሸላሚ ለሆነ የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን ብር ፩፻ ሺ እና በርዕሰ ብሔሩ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

፭· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (መ) እና (፫) ለሠራዊት አሃድና ቡድንም ተፈጻሚ ይሆናል ፤ ስለሆነም በትውልድ ሥፍራ ምትክ ጀግንነቱ የተፈጸመበት ሥፍራ ይሆናል ።

፴፱· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ

፩· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ በተሰለፈበት አውደ ውጊያ የዘወትር ወታደራዊ ግዳጅ አፈጻጸም ከሚጠይቀው በላይ እጅግ በጣም የሚያኮራ ጀግንነት ለፈጸመ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነው።

፪· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው፡

ሀ) በሕይወት ያለ ከሆነ ብር ፳ ሺ የአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጠዋል ፤ ከሞተም በጡረታ ሕግ በተመለከተው መጠን መሠረት ለወራሾቹ ብር ፳ ሺ ይከፈላል ፤

ለ) በብሔራዊ በዓል አከባበር ሥነ–ሥርዓት ወቅት ለከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል ፤

ሐ) በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል ።

፫· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ሁለት ጊዜ የተሸለመ ሰው በትውልድ ሥፍራው ትምህርት ቤት ፤ ሆስፒታል ፤ መንገድ ፤ አደባባይ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መጠሪያ በስሙ ሊሰየምለት ይችላል ።

2) The dimension, shape and substance of the Medals, Ribbon and Certificates enumerated under sub-Article (1) of this Article shall be prescribed by directives of the Council of Ministers.

*38. The Medal of the Victory of Adwa*

1) The Medal of the Victory of Adwa is the highest award that may be bestowed upon an Ethiopian individual, military unit or group that has performed unparalleled feats of bravery in a battlefield.

2) Awardee of the Medal of the Victory of Adwa:

(a) shall be entitled to a one time payment of 25,000 Birr. Where he has died his survivors shall be entitled to same in accordance with the proportion specified in the Pension Law;

(b) shall take a seat in the place reserved for high government officials during any public ceremony;

(c) shall receive a special identity card autographed by the Head of State;

(d) may have a school, a hospital, an avenue or a public square or any other similar memorial, in his birth place, named after him.

3) A school, a hospital, an avenue, a bridge, a public square or any other similar memorial in the Federal Capital City may be named after an individual who has been awarded the Medal of the Victory of Adwa for the second time. In addition a statute may be erected for such an individual.

4) A military unit or group awarded with the Medal of the Victory of Adwa shall be entitled to Birr 100,000 and a special certificate autographed by the Head of State.

5) Sub-Article 2(d) and (3) of this Article shall apply to the military unit and group, with birth place substituted by the battlefield of its exploits.

*39. The Medal of Heroism 1st Rank*

1) The Medal of Heroism 1st Rank is an award that may be bestowed upon an Ethiopian individual, military unit or group that has, beyond the call of ordinary duty, achieved very honorable feats of bravery in a battlefield.

2) Awardee of the Medal of Heroism 1st Rank:

(a) shall be entitled to a one time payment of 20,000 Birr. Where he has died his survivors shall be entitled to same in accordance with the proportion specified in the Pension Law;

(b) shall take a seat in the place reserved for high government officials during any public ceremony at the place where the ceremony is held;

(c) shall receive a special identity card autographed by the Commander-in-Chief of the Armed Forces.

3) A school, a hospital, an avenue or a public square or any other similar memorial in his birth place may be named after an individual who has been awarded the Medal of Heroism 1st Rank for the second time.

moj Ministry of justice



፬· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ሦስት ጊዜ የተሸለመ ወይም የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ እና የአድዋ ድል ሜዳይ የተሸለመ ሰው በፌዴራል ዋና ከተማ ትምህርት ቤት ፡ ሆስፒታል፡ መንገድ ፡ አደባባይ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መጠሪያ በስሙ ሊሰየምለት ይችላል።

፭· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ተሸላሚ ለሆነ የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን ብር ፹ ሺ እና በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ።

፮· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ለሠራዊት አሃድና ቡድንም ተፈጻሚ ይሆናል ፡ ስለሆነም በትውልድ ሥፍራ ምትክ ጀግንነቱ የተፈጸመበት ሥፍራ ይሆናል ።

፵· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ

፩· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ በተሰለፈበት አውደ ውጊያ የዘወትር ወታደራዊ ግዳጅ አፈጻጸም ከሚጠይቀው በላይ በጣም የሚያኮራ ጀግንነት ለፈጸመ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነው ።

፪· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው ፡

ሀ) በሕይወት ያለ ከሆነ ብር ፲፭ ሺ የአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጠዋል ፡ ከሞተም በጡረታ ሕግ በተመለከተው መጠን መሠረት ለወራሾቹ ብር ፲፭ ሺ ይከፈላል ፡

ለ) በብሔራዊ በዓል አከባበር ሥነ–ሥርዓት ወቅት ለከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል ።

ሐ) በጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል ።

፫· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ ተሸላሚ ለሆነ የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን ብር ፵ ሺ እና በጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ።

፵፩· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ

፩· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ በተሰለፈበት አውደ ውጊያ የዘወትር ወታደራዊ ግዳጅ አፈጻጸም ከሚጠይቀው በላይ የሚያኮራ ጀግንነት ለፈጸመ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነው ።

፪· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው፡

ሀ) በሕይወት ያለ ከሆነ ብር ፲ ሺ የአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጠዋል ፡ ከሞተም በጡረታ ሕግ በተመለከተው መጠን መሠረት ለወራሾቹ ብር ፲ ሺ ይከፈላል ።

ለ) በጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል ።

፫· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ሦስት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ የተሸለመ ሰው በብሔራዊ በዓል አከባበር ሥነ–ሥርዓት ወቅት በተለይ በሚወሰንለት የክብር ሥፍራ ይቀመጣል ።

፬· የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ተሸላሚ ለሆነ የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን ብር ፵ ሺ እና በጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

4) A school, a hospital, an avenue or a public square or other similar memorial in the Federal Capital City may be named after an individual who has been awarded the Medal of Heroism 1st Rank for the third time or the Medal of Heroism 1st rank and the Medal of the Victory of Adwa.

5) Awardee of the Medal of Heroism 1st Rank is entitled to Birr 80,000 and shall receive a special identity card autographed by the Commander-in-Chief of the Armed forces.

6) Sub-Article (3) and (4) of this Article shall be applicable to a military unit and group; with birth place substituted by the place where the heroic deed was performed.

*40. The Medal of Heroism 2nd Rank*

1) The Medal of Heroism 2nd Rank is an award that may be bestowed upon an Ethiopian individual, military unit or group that has, beyond the call of ordinary duty, achieved honorable feats of bravery in a battlefield;

2) Awardee of the Medal of Heroism 2nd Rank:

(a) shall be entitled to a one time payment of 15,000 Birr. Where he has died, his survivors shall be entitled to same in accordance with the proportion specified in the Pension Law;

(b) shall take a seat in the place reserved for high government officials during any public ceremony at the place where the ceremony is held;

(c) shall receive a special identity card autographed by the General Chief of Staff.

3) A military unit or group awarded with the Medal of Heroism 2nd Rank is entitled to Birr 40,000 and shall receive an identity card autographed by the General Chief of Staff.

*41. The Medal of Heroism 3rd Rank*

1) The Medal of Heroism 3rd Rank is an award that may be bestowed upon an Ethiopian individual, military unit or group that has, beyond the call of ordinary duty, achieved commendable feats of bravery in the battlefield;

2) Awardee of Medal of Heroism 3rd Rank:

(a) shall be entitled to a one time payment of 10,000 Birr. Where he has died, his survivors shall be entitled to same in accordance with the proportion specified in the Pension Law;

(b) shall receive a special identity card autographed by the General Chief of Staff.

3) Awardee of Medal of Heroism 3rd Rank for the third or more time shall take a seat in the place reserved for high government officials during any public ceremony at the place where the ceremony is held;

4) A military unit or group awarded with the Medal of Heroism 3rd Rank is entitled to Birr 40,000 and a special identity card autographed by the General Chief of Staff;

moj
Ministry of justice



፵፪. የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ባለዘንባባ

፩. የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ባለዘንባባ በኢትዮጵያ ሠላምና ዲሞክራሲን ለማስፈን ከደርግ ፡ ኢሠፓ መንግሥት ጋር ከ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. እስከ ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ድረስ በተጥቀ ትግሉ ከአሥር ዓመት ያላነሰ ተሳትፎ ላለው ታጋይ የሚሰጥ ሽልማት ነው ።

፪. የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ባለዘንባባ የተሸለመ ሰው በጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል ።

፵፫. የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ያለዘንባባ

፩. የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ያለዘንባባ በኢትዮጵያ ሠላምና ዲሞክራሲን ለማስፈን ከደርግ ኢሠፓ መንግሥት ጋር ከ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. እስከ ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ድረስ በተጥቀ ትግሉ ከአሥር ዓመት በታች ተሳትፎ ላለው ታጋይ የሚሰጥ ሽልማት ነው ።

፪. የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ያለዘንባባ የተሸለመ ሰው በጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል ።

፵፬. የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ

፩. የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ በአእምሮ ሥራ ወይም በፈጠራ ወይም በማናቸውም መስክ ለመከላከያ ሠራዊት ተልዕኮ መሳካት የላቀና ወደር የሌለው ውጤት ላስገኘ ሰው ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነው ።

፪. የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ የተሸለመ ሰው ፡

ሀ) ብር ፲ ሺ የአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጠዋል ፤

ለ) በብሔራዊ በዓል አከባበር ሥነ ሥርዓት ወቅት ለከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል ፤

ሐ) በሀገር መከላከያ ሚኒስትሩ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጣል ።

፫. የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ ለተሸለመ የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን ብር ፵ ሺ እና በመከላከያ ሚኒስትሩ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል'።

፵፭. የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ

የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ በሥነ ምግባሩና በወታደራዊ ሥነ-ሥርዓት የጐላ እንከን የሌለበትና በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ከሃያ አምስት ዓመታት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ የሠራዊት አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው ።

፵፮. የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ

የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ በሥነ ምግባሩና በወታደራዊ ሥነ-ሥርዓት የጐላ እንከን የሌለበትና በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ከአሥራ አምስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ የሠራዊት አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው ።

፵፯. የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ

የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ በሥነ ምግባሩና በወታደራዊ ሥነ-ሥርዓት የጐላ እንከን የሌለበትና በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ከአሥር ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ የሠራዊት አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው ።

፵፰. ዓለም አቀፍ የሰላም ማስጠበቅ ሜዳይ

፩. ዓለም አቀፍ የሠላም ማስጠበቅ ሜዳይ ከኢትዮጵያ ውጭ ከ፺ ቀናት ላላነሰ በዓለምአቀፍና አህጉራዊ የሠላም ማስጠበቅ ተግባር ለተሳተፈ ሰው የሚሰጥ ሽልማት ነው ።

፪. ዓለም አቀፍ የሠላም ማስጠበቅ ሜዳይ የተሸለመ ሰው በጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል ።

42. *The Medal with Palm Leaf for Participation in the Armed Struggle*

1) The Medal with Palm Leaf for Participation in the Armed struggle shall be awarded to all fighters who served no less than ten years in the struggle (1975-May 28/1991) to remove the Derg regime and establish peace and democracy in Ethiopia.

2) An awardee of the Medal with Palm Leaf for Participation in the Armed Struggle shall receive a special identity card autographed by the General Chief of Staff.

43. *The Medal without Palm Leaf for Participation in the Armed Struggle*

1) The Medal without Palm Leaf for Participation in the Armed Struggle shall be awarded to all fighters who served less than ten years in the struggle (1975-May 28/1991) to remove the Derg regime and establish peace and democracy in Ethiopia.

2) An awardee of the Medal without Palm Leaf for Participation in the Armed Struggle shall receive a special identity card autographed by the General Chief of Staff.

44. *The Medal of Distinguished Labour*

1) The Medal of Distinguished Labour is an award that may be bestowed upon a person, military unit or group that has through mental labour, or way of invention or in any other field, scored unparalleled achievement for the mission of the Defence Forces.

2) Awardee of the Medal of Distinguished Labour shall:

(a) be entitled to Birr 10,000;

(b) take a seat in the place reserved for high government officials during any public ceremony at the place where the ceremony is held;

(c) receive a special indentity card autographed by the Minister of National Defence.

3) Military unit or group of awardee of the Medal of Distinguished labour is entitled to Birr 40,000 and shall receive a special indentity card autographed by the Defence Minister.

45. *The Medal of Military Service 1st Rank*

The Medal of Military Service 1st Rank is an award that may be bestowed upon any member of the Defence Forces who is reputed for his spotless record of conduct and military discipline and has served in the Defence Forces for not less than twenty five years.

46. *The Medal of Military Service 2nd rank*

The Medal of Military Service 2nd Rank is an award that may be bestowed upon any member of the Defence Forces who is reputed for his spotless record of conduct and military discipline and has served for not less than fifteen years in the Defence Forces.

47. *The Medal of Military Service 3rd rank*

The Medal of Military Service 3rd Rank is an award that may be bestowed upon any member of the Defence Forces who is reputed for his spotless record of conduct and military discipline and has served for not less than ten years in the Defence Forces.

48. *The Medal of International Peace Keeping*

1) The Medal of International Peace Keeping is awarded to a person who has participated in international peace-keeping duties abroad for not less than 90 days;

2) Awardee of the Medal of International Peace Keeping shall receive a special indentity card autographed by the General Chief of Staff.

Ministry of justice
moj


፵፱. የአውደ ውጊያ ቁስለኛ ሜዳይ

፩. የአውደ ውጊያ ቁስለኛ ሜዳይ በአውደ ውጊያ ተሰልፎ የመቁሰል አደጋ ለደረሰበት ሰው የሚሰጥ ሽልማት ነው።

፪. የአውደ ውጊያ ቁስለኛ ሜዳይ የተሸለመ ሰው በክፍለ ጦር ወይም በኮር አዛዥ ወይም በተመጣጣኝ ደረጃ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል ።

፶. የውትድርና አገልግሎት ሪባን

የውትድርና አገልግሎት ሪባን ለሕገመንግሥቱ ታማኝ በመሆን በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ለተሰጠ ለእያንዳንዱ አምስት ዓመት አገልግሎት የሚሰጥ ሽልማት ነው ።

፶፩. የውጊያ ተሳትፎ የምስክር ወረቀት

የውጊያ ተሳትፎ የምስክር ወረቀት በመንግሥት በታወቀና በታወጀ ወታደራዊ ስምሪት (ዘመቻ) ለተሳተፈ ሰው ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነው ።

፶፪. የሜዳይ ተሸላሚ የሚያገኘው ተጨማሪ ልዩ መብት

በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ (፩)(ሀ)–(ሰ) ፣ (ተ) ወይም (ቸ) የተመለከተውን ማንኛውም ሜዳይ የተሸለመ ሰው ፤

፩. በመንግሥት ሆስፒታሎችና የሕክምና ተቋሞች ውስጥ ነፃ ሕክምና ያገኛል ፤

፪. በመንግሥት የትምህርት ተቋሞች ውስጥ ለመማር ቅድሚያ ያገኛል ፤

፫. በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ፣ ድርጅቶችና ተቋሞች ውስጥ ችሎታው ለሥራ መደቡ ተስማሚ ሆኖ ሲገኝ የመቀጠር ቅድሚያ ይሰጠዋል ።

፶፫. ለሜዳይ ሽልማት የሚያበቃ ሥራ ሠርቶ ስለሞተ ሰው

፩. ለሜዳይ ሽልማት የሚያበቃ ሥራ ሠርቶ የሞተ ሰው አግባብ ያለው ሜዳይ በስሙ ይመዘገባል ።

፪. ሜዳዩ ለታላቅ ልጁ ይሰጣል ። ልጅ ከሌለው ለባለቤቱ ፤ ባለቤት ከሌለው አግባብ ባለው የውርስ ሕግ መሠረት ለውርስ ባለመብቱ ይሰጣል ።

፶፬. ከውጪ አገር ሜዳይ ወይም ሌላ ሽልማት ስለመቀበል

ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ከአገር መከላከያ ሚኒስቴር ፈቃድ ሳያገኝ ከውጭ አገር ሜዳይ ወይም ሽልማት ሊቀበል አይችልም ።

፶፭. ሜዳይ ፣ ሪባን ወይም የምስክር ወረቀት መልሶ ስለመውሰድ

ተሸላሚው፣

፩. ሜዳዩ ፣ ሪባኑ ወይም የምስክር ወረቀቱ የተሰጠው በተሳሳተ ማስረጃ መሆኑ ሲታወቅ ፣ ወይም

፪. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከቁጥር ፪፻፶፱–፪፻፷፭ የተመለከቱትን ወንጀሎች መፈጸሙ በፍ/ቤት ውሣኔ ሲረጋገጥ፣

የተሰጠው ሜዳይ ፣ ሪባን ወይም የምስክር ወረቀት ይወሰድበታል ።

፶፮. የሜዳዮች ደረጃ ቅደም ተከተል

የሜዳዮች ደረጃ ቅደም ተከተል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯(፩) በተመለከተው ዝርዝር ቅደም ተከተል መሠረት ይሆናል።

49. *The Medal of the Wounded*

1) The Medal of the Wounded is an award that may be bestowed upon a person who has been wounded in a battlefield.

2) An awardee of the Medal of the Wounded shall receive a special identity card autographed by a divisional or corps commander or by an officer of equivalent rank.

50. *Military Service Ribbon*

The Military Service Ribbon is awarded to members of the Defence Forces for every 5 years of service given in loyalty to the Constitution.

51. *Combat Certificate*

Combat Certificate is an award to be given to a person, military unit or group having participated in a campaign initiated and proclaimed by the government.

52. *Additional Privileges of Medal Awardees*

Without prejudice to other Articles of this Proclamation, an awardee who is bestowed with any of the medals enumerated under Article 37/1/(a)–(g), (k) or (i) shall:

1) receive free medical treatment in state owned hospitals and health centres;

2) be given priority to pursue education in state owned educational institutions;

3) be given priority to employment where the qualification satisfies the job descriptions required by government offices, organizations and establishment for a given position.

53. *Posthumous Award of Medals*

1) The appropriate medal shall be registered in the name of a person who dies after having accomplished a deed.

2) The medal shall be given to his elder descendant; in the absence of a descendant to his spouse; in the absence of a spouse to his heir under the relevant law of succession.

54. *Receiving Foreign Medals or Other Prizes*

Any member of the Armed Force shall not receive a medal or other prize without permission from the Ministry.

55. *Deprivation of Awards*

The Medal, Ribbon or Certificate shall be withdrawn from the awardee, where:

1) it is discovered that the Medal, Ribbon or Certificate was bestowed upon the awardee on the basis of wrong evidence; or

2) such an awardee has been found guilty by a court for offenses provided for in Articles 259-265.

56. *Rank of Medals*

The order of rank of medals shall be in accordance with Article 37(1) of this Proclamation.

moj

Ministry of justice



፶፯. <u>የሜዳዮችና ሪባኖች አሰጣጥ ሥርዓትና አለባበስ</u>

በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ሜዳዮችና ሪባኖች አሰጣጥ ሥርዓትና አለባበስ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ ይወሰናል ፡፡

፯. የአዋጁ የቀድሞው ክፍል ስድስት ክፍል ሰባት ሆኖ አንቀጽ ፴፯–፴፱ እንደ ቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፶፰–፷ ሆነዋል ፡፡

፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

57. *Award and Wearing of Medals and Ribbons*

The award and wearing of medals and ribbons shall be prescribed in accordance with directives to be issued by the Council of Ministers.

7. Part Six of the Defence Forces Proclamation has become Part Seven and Articles 37-39 have become Articles 58-60, respectively.

3. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 30th day of June, 1998.

Done at Addis Ababa, this 30th day of June, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE